# ይድረስ ለቀድሞ የወያኔ አመራር ቡድን አባሎች


## አክሱም ሆቴል

### መቀሌ፣ የትግራይ ክልል፣ ኢትዮጵያ

**ክፍል ሁለት፡-**

**በሃሰተኛ ውንጀላ የመሳሪያ እና የኢኮኖሚ ማዕቀብ በማስጣል በኤርትራ ላይ ያደረሳችሁት ጉዳት**

“የኢሳይያስን ጉሮሮ ማነቅ የሚቻለው አሜሪካና ሌሎች ተባብረው ኤርትራ ላይ የገንዝብ ማዕቀብ ሲጥሉ እንዲሁም ከሌሎች አገራት በተለይም ከቃጣር መንግሥት የምታገኘው የገንዝብ እርዳታ ሲቋረጥ ይኾናል። ሌላው ለመንግሥት ከፍተኛ የገቢ ምንጭ የሆነውን አሜሪካ ከሚገኙ ኤርትራውያን የሚላከውን ገንዘብ ማስቆም ነው”። መለስ ዜናዊ (ግንቦት 2009 እ.ኤ.አ)



1. በክፍል 1 መጨረሻ ላይ ያስፈርኩት የድንበር ኮሚሽኑን ውሳኔ ለማስቀየር በእናንተ ክስ አቅራቢነት የአሜሪካ መንግሥት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የፀጥታ ምክር ቤት አባላት ላይ ያደረገውን ከፍተኛ ጫና የሚያወሳ ነበር። በወቅቱ በአሜሪካን ስቴት ዲፓርትመንት የአፍሪካ ጉዳይ ከፍተኛ ባለሥልጣን የነበሩት ጃንዳይ ፍሬዘር በታኅሣስ 2006 (በእ/ኤ/አ) ወደ ኢትዮ-ኤርትራ ድንበር ዘልቀው አዲግራትንና ዛላምበሳን ጎበኙ። ቀጥለውም በኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ሄሊኮፕተር ባድመ ደርሰው በኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት አባል አስተርጓሚነት (ምናለ ገለልተኛ የሆነ አስተርጓሚ ከኤምባሲያቸው ቢጠቀሙ) በቅድሚያ በናንተው ከተመረጡ የባደመ ነዋሪዎች ጋር አጭር ቆይታ አደረጉ። ከአጭር ቆይታ በኋላ፡ “የባድመ ነዋሪዎች ከፍተኛ የኢትዮጵያዊነት ስሜትና ማንነት እንዳላቸው ተገንዝቢያለሁ። አቶ መለስ ዜናዊም ለምን የድንበር ኮሚሽኑን ውሳኔ ለመቀበልና ለመተግበር እንደተቸገረ ጥሩ ግንዛቤ አግኝቻለሁ” ሲሉ ገለጹ። ቀጥለውም የተባበሩት መንግሥታት የሰላም አስከባሪ ሚሽን (UNMEE) ከፍተኛ ባለሥልጣን ጆሴፍ ሳጉየላ ጋር ሲገናኙ “አከራካሪ የሆነውን ባድመን ለኤርትራ የሰጠውን የድንበር ኮሚሽን ውሳኔ የባድመ ነዋሪዎች ኢፍትሐዊና ሚዛን የጎደለው ነው በማለት አጥብቀው እንደሚቃወሙት በጉብኝቱ ሊረዱ መቻላቸውን፤ ስለዚህ “ጉዳዩ የሚመለከታችው ሁሉም አካላት የድንበር ኮሚሽኑ ጭምር አቋማቸውን ማላላት ይኖርባቸዋል” የሚል ድምዳሜ ሰጡ። የሚያሳዝነው አሜሪካዊቷ ከፍተኛ ዲፕሎማት ጉዳዩ የብዙ ሰው ሕይወት የቀጠፈ መሆኑን ባለ መገንዘባቸው ብቻ ሳይሆን ስለጉዳዩ ጥልቅ ዕውቀት ያላቸው ሌሎች ዲፕሎማቶች ለዓመታት ሞክረው ያልቻሉትን በ30 ደቂቃ ጉብኝት ድምዳሜ ላይ መድረሳቸው ነው። የኤርትራ መንግሥት ጉብኝቱንና የሰጡትን አስታያይት በጥብቅ ወቀሰ።

2. አምባሳደር ላጉየላም “በባድመ ያነጋገርኻቸው ነዋሪዎች በመንግሥት የተመለመሉና የመንግሥትን አቋም የሚግልጹ ናቸው፤ ሆኖም የድንበሩ ውሳኔ ሳይተገበር በሁለቱ ሃገሮች መካከል ስለ ሌላ ጉዳዮች መነጋገር የሚችሉ አይምስለኝም። የድንበር ውሳኔው በተግባር ላይ ከዋለ ግን የሁለቱ ሃገሮች የሰላም ሂደት ሊሻሻል እንደሚችልና የአሰብን ወደብ ኢትዮጵያ ልትጠቀምበት እንደምትችል ኤርትራ ገልጻልኛለች” የሚል አስተያየት ሰጡ። ጃንዳይ ፍሬዘር ከባድመ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው ከጠ/ሚንስትር መለስ ዜናዊ ጋር ስብሰባ ተቀመጡ። ስለጉብኝቱ ከተነጋገሩና ሃሳብ ለሃሳብ ከተቀያየሩ በኋላ የድንበሩ ኮሚሽኑን ውሳኔ ለማስቀየር መወሰድ ሰላለባቸው እርምጃዎች ተስማሙ። ይኽ ሴራ (በክፍል 1 እንደተገለጸው) በአምባሳደር ቦልተን እምቢተኛነት ልክ እንደሌሎቹ ሙከራዎች ፍሬ አልባ ሆኖ ቀረ።

3. በመቀጣል የኤርትራን መንግሥት ከሥልጣን ለማስውገድ ሦስት ዘዴዎች ተጠቀማችሁ። አንደኛ ኤርትራውያን ወጣቶች ላይ በማነጣጠር አገር ለቀው ወደ ኢትዮጵያና ሱዳን እንዲወጡ በማባበል “ወደ ስደተኛ ካምፕ ከመጣችሁ በአጭር ጊዜ አሜሪካ፣ አውስትራሊያና አውሮፓ ትሄዳላችሁ” የሚል ፕሮፓጋንዳ ነዛችሁ። ዋናው ዓላማው የኤርትራ መከላከያ ሰራዊት እንዲዳከም ሲሆን፣ ድንበር ተሻግረው የስደተኞች ካምፕ የደረሱ ወጣቶችን የኤርትራ መታወቂያ ካርዳቸውን ነጠቃችሁ። በቀማችሁት የመታወቂያ ወረቀት በመጠቀም የትግራይ ተወላጆችን በኤርትራውያኑ ስም ወደ አሜሪካ፣ አውሮፓ፣ አውስትራሊያ በሠፈራ ፕሮግራም ለመላክ እንደተጠቀማችሁበት የአደባባይ ምሥጢር ነው።

4. ሁለተኛ የተቃዋሚ ቡድኖችን አደራጃችሁና አስታጠቃችሁ። ቁጥራቸውም ወደ ዐሥራ ሦስት ደርሰው ነበር። ሦስቱ እስላማዊ ግንባሮች እና ሁለት የብሔር ድርጅቶች ሲሆኑ፣ ስምንቱ ከቀድሞ ጀብሃ የወጡ እና አዳዲስ ሕብረ-ብሔራዊ ድርጅቶች ናቸው። የተቃዋሚ ቡድኖቹ ዋና ዓላማቸው ፕሬዝዳንት ኢሳይያስ አፈወርቂን ከሥልጣን ለማውረድ እንደሆነ በወቅቱ በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር ለነበሩት ያማሞቶ ገልጸዋል።

በኤርትራና በውጭ አገር በሚገኙ ኤርትራውያን ዕይታ የተቃዋሚ ቡድኖቹ የወያኔ መጫወቻ አሻንጉሊት ሆነው በመቆጠራቸው ይኽም በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት ከፍተኛ ችግር እንደፈጠረባቸውም ለያማሞቶ በግልፅ ተናገሩ። የአሜሪካው አምባሳደር አዲስ አበባ በተደረገው የተቃዋሚዎች ጉባኤ በታዛቢነት ለመሳተፍ ወይንም መልዕክት ለማስተላለፍ ፍላጎት ማሳየታቸው አስገራሚ ነበር። ለዚህም የስቴት ዲፓርትመንትን ፍቃድ ጠይቀዋል።

5. በስደተኞች ካምፕ የሚገኙትን የሳዋ ስልጣኝ ወጣቶች ለመመልመል አቶ ስብሃት ነጋ የስደተኞች ካምፕ ሄደው ገለጻ ሲያደርጉ ”ብዙዎቻችሁ በሳዋ ወታደራዊ ሥልጠና የቀሰማችሁ ወጣቶች ስለሆናችሁ የኤርትራ ተስፋ እናንተ ናችሁ። ስለዚህ ተደራጅታችሁ የኤርትራን መንግሥት ለመገልበጥ ተንቀሳቀሱ፣ አስፈላጊውንም እርዳታ እናደርግላችኋለን” አሉ፡፡ ቀጥለውም የአሜሪካ መንግሥት የሻዕቢያን መንግሥት ለማዳከም ኤርትራ ላይ ከፍተኛ የሆነ ወታደራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ዲፕሎማሲያዊ ማዕቀብ (sanction) ለማድረግ መዘጋጀቱን ገለጹ። ወያኔም ለተቃዋሚ ድርጅቶች አስፈላጊውን መሳርያና ሥልጠና በመስጠት በአጭር ጊዜ ውስጥ የሻዕብያን መንግሥት ከሥልጣን ለማስወገድ እንደተዘጋጀም በስደተኛ ካምፕ ላሉት ኤርትራውያን ወጣቶች ነገረ።

የዚህ መዳረሻ ዓላማው የኤርትራን ▶

በብሔር ላይ የተመሠረተ የክልል ፌዴራሊዝም ሥርዓት መመስረት ነው። ወጣቶቹም ይኽን በመገንዘብ ጭምር ሊሆን ይችላል በድፍረት "እኛ ከአገር የወጣነው ውጭ ሃገር ሄደን ኑሯችንን ለማሻሻል እንጂ ጦር መሳሪያ አንስተን ያስተማረች ሀገራችንን ለመውጋት አይደለም" የሚል መልስ ሲሰጡ ሽማግሌው አቦይ ስብሀት በመናደድ "የሻዕቢያ መርፌ የተወጋችሁ ለመሆናችሁ ማረጋግጫ ነው" በማለት ቦታውን ለቀው ሄዱ። የቀድሞ የወያኔ መሪዎች ማወቅ የተሳናችሁ ትልቅ ምሥጢር ስለሳዋ ሥልጠና ማዕከል ነው። በሳዋ ከሁሉም ብሄሮች የተወጣጡት ምልምል ወጣቶች ከአካዳሚያዊና ወታደራዊ ሥልጠና ከመቅሰም ባሻገር በ18 ወራት ሳዋ ቆይታቸው የእርስ በርስ መከባበርና መቻቻል፣ የአብሮ መኖር አመለካከት ማዳበራቸውና አንድነታቸው ነው። ለኤርትራ ሉዓላዊነት መከበርና ለሀገሪቱ ሠላምና መረጋጋት ሳዋ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጉ የሚያጠያይቅ አይደለም።

**6.** ሦስተኛ የኤርትራን መንግሥት ከሥልጣን ለማስወገድ እንዲረዳ በሀሰት ክስ የመሳርያና የኢኮኖሚ ማዕቀብ ማስጣል።

የፕሬዝደንት ኢሳይያስ መንግሥት ለሶማሊያው ሽብርተኛ ቡድን አል-ሸባብ ወታደራዊ ትጥቅ ያቀብላል ብላችሁ ኤርትራ ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ተማጸናችሁ። በፕሬዚደንት ባራክ ኦባማ አስተዳደር በተባበሩት መንግሥታት የአሜሪካ አምባሳደር ሆነው በወቅቱ የተሾሙት አምባሳደር ሱዛን ራይስ ለዚህ ዋናው ተዋናይ ነበሩ። በ2009 የኢትዮጵያ ጉብኝታቸው ከጠ/ሚኒስተር መለስ ዜናዊ ጋር ጋር ረጅም ሰዓት የፈጀ ስብሳባ ተቀመጡ። አቶ መለስ በቀጠናው ስለሚገኙት እያንዳንዱ አገር (ኤርትራ፣ ሱዳን፣ ደቡብ ሱዳንና ሶማልያ) ፖለቲካዊ ሁኔታ ዝርዝር ትንታኔ ሰጡ። የኤርትራ መንግሥትና ኤርትራ የምታስታጥቀው የሶማሊያው ሽብርተኛ ቡድን አል-ሸባብ ለኢትዮጵያ ፀጥታ ዋናው ስጋት መሆኑንና ይኽን ተግባር ለመቅጨት መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች በዝርዝር አስቀመጡ።

**7.** ከአቶ መለስ ምክሮች በተለይ ትኩረቱን የሳበው "የኢሳይያስን ጉሮሮ ማነቅ የሚቻለው አሜሪካና ሌሎች ተባብረው ኤርትራ ላይ የገንዘብ ማዕቀብ ሲጥሉ እንዲሁም ኤርትራ ከሌላ አገሮች በተለይ ከቃጣር የምታገኘውን የገንዘብ እርዳታ እንዲቋረጥ ማድረግና ለመንግሥት ከፍተኛ የጋቢ ምንጭ የሆነውን አሜሪካ ከሚገኙ ኤርትራውያን የሚላከውን ገንዘብ ማስቆም"፣ ቀጥለውም "አሜሪካ በምሥጢር ኢሳይያስን በማነጋገር ጠባዩን እንዲቀይር ለማድረግ መሞከር፣ ካልሆነ የእገዳ ዱላ እንዳሚጣልበት አሳስቦ የሚሰጠውን መልስ ማየት፣ ማንኛውም በይፋ የሚሰጥ መግለጫ ይሁን ማስፈራርያ ከኢሳያስ ጋር ሊሰራ አይችልም። የማያቋርጥ ወታደራዊ ጫናና ከባድ የኢኮኖሚ ማዕቀብ ኤርትራ ላይ ከተደረገ ግን ግፊቱ ውጤታማና የተፈለገውን ውጤት ሊያመጣ ይችላል"

ኤርትራን ለማንበርከክ ይኽን ሃሳብ ነበር መለስ ዜናዊ ለአሜሪካዊቷ ሱዛን ራይስ ያማከሩት። ይኽ ከሆነ ከጥቂት ወራት በኋላ የኤርትራ መንግሥት በሶማሊያ አልሸባብን ይረዳል። ከጅቡቲ ጋር አወዛጋቢ ከሆነው ድንበር ወታደሮቻን ለማወጣት ፈቃደኛ አይደለም በሚል የሃሰት ክስ በታኅሣስ 2009 (እ/ኤ/አ.) የተባበሩት መንግሥታት ሰኩሪቲ ካውንስል በኤርትራ ላይ የመሳርያና ኢኮኖሚያዊ ማዕቀብ ጣለ። ይኽ በቁጥር 1907 የሚታዋቀው ማዕቀብ የጦር መሣሪያ ግዢ ዕቀባ፣ የከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ላይ የጉዞ እገዳና የአንዳንድ የሀገሪቱን የፖለቲካና ወታደራዊ ባለሥልጣናት ሀብት ማገድን ያጠቃልላል።

**8.** ይኽ ኤርትራ ላይ የተጫነው ዐሥር ዓመታት ያሥቆጠረው እገዳ በአገራችን ኢኮኖሚና በመሠረተ ልማት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማድረሱ የሚያጠያይቅ ጉዳይ አይደለም። ያስጣላችሁብን እገዳም ሆነ የተቃዋሚ ቡድኖችን ማስታጠቅ የፈለጋችሁትን የመንግሥት ግልበጣ ሳይመጣ እንደሌሎቹ እርምጃዎች ሁሉ ይኽም ከሽፎ እናንተ ቀድማችሁ የአራት ኪሎውን ቤተመንግሥት ተነጥቃችሁ ወደ መቀሌ ሸሻችሁ። ዋናው ሕልማችሁ በአንድ ኤክስፐርት አገላላጽ "Somalizaiton of Eritrea" ማለት የኤርትራ መንግሥትን ኣዳክሞ ከሥልጣን ማስወገድና ኤርትራን እንደሶማሊያ በመፈረካከስ የጅሃዳዊ ሽብርተኝነት መናኸርያ ማድረግ ነበር። ግን አልተሳካላችሁም!! ዋናው ምክንያቶች በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰማዕታት በመክፈል የኤርትራ ሕዝብ ሉዓላዊነቱን ለማስከበር ስለመከተ፣ በአስቸጋሪ ጊዜያት ሕዝቡ ግፊትን የመቋቋም ችሎታውንና በቁርጠኝነቱ በዓላማው ጸንቶ የመቆየት ባህሉን በመጠበቁ ነበር። በኢኮኖሚና ማኅበራዊ ሴክተሮች መንግሥት የወሰዳቸው "ቀበቶ የማጥበቅ" ወሳኝ እርምጃዎችም ኤርትራ በእናንተ ሳቢያ የተጋፈጠችውን መከራ እንድትሻገር አድርጓታል።

**9.** የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ የድንበር ኮሚሽንን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ተቀበለው በኤርትራ ታሪካዊ ጉብኝት አደረጉ። በሐምሌ 9 ቀን 2018 (እ.ኤ.አ) የኤርትራው ፕሬዝደንት ኢሳይያስ አፈወርቂና ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የሰላም ውል አሥመራ ተፈራረሙ። በዚህም በሁለቱ አገራት መካከል ለሃያ ዓመታት የዘለቀውን ጦርነት ማብቃቱን አወጁ። እናንተ ለዐሥራ ስምንት ዓመት መቀበል አሻፈረኝ ያላችሁትን የድንበሩን ውሳኔ በአጭር ጊዜ በመቀበላቸውና በሁለቱ አገሮች መካከል ለሰፈነው የሰላም ተስፋ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በማድነቅ ለዶ/ር ዐቢይ አሕመድ የኖቤል የሰላም ሽልማት ሰጣቸው።

የሶማሊያ ፕሬዝዳንት ፎርማጆ በዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ደጋፊነት ለተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ም/ቤት ማዕቀቡን እንዲያነሳ ጥሪ አቅርበው ለዐሥር ዓመት ኤርትራ ላይ ያስጣላችሁት ማዕቀብ በየካቲት 2019 (እ/ኤ.አ) ተነስቷል። ቀጥሎም በትግራይ ያቋቋማችኋቸው የስደተኛ ካምፖች በዶ/ር ዐቢይ ተዘጉ። ምንም ቁም ነገር ሳያደርጉ ለዐሥራ ስምንት (18) ዓመታት እናንተ ሥር ተወሽቀው የኖሩት የተቃዋሚ ቡድኖች (ከእናንተው ጋር መቀሌ ከሰፈሩት ሁለት በቀር) ጓዛቸውን ጠቅልለው ኢትዮጵያን ለቀው ወጥተዋል። እነዚህ በ2018 በአሥመራ የተፈረመው የሰላም ስምምነት ተጨባጭ የመጀመርያ ውጤቶች ናቸው።

**10.** ከአራት ኪሎ ቤተ መንግሥት በሕዝቡ ከፍተኛ ግፊት ሥልጣን ለቃቹህ መቀሌ ከሰፈራችሁም በኋላ ከኤርትራ ጋር ያለው ፍጥጫ አሁንም እንደቀጠለ ነው። ዘላቂ ሰላም ለመፍጠር የተዘጋጃችሁ አለመሆናቸውም በግልጽ ይታያል። ባላችሁበት ሁኔት ሁለት አማራጮች ያላችሁ ይመስለኛል። አንደኛው ባለፉት ሃያ ዓመታት በያዛችሁት እምቢታ በመቀጠል የኤርትራ መንግሥት ከፌደራል መንግሥት ጋር በመተባብር በጦር ሊያጠቃን ነው በሚል የሃሰት ፕሮፓጋንዳ የትግራይን ሕዝብ እንደ ሆስቴጅ በመያዝ ወደ አላስፈላጊ ዳግማዊ ደም መፋሰስ መግባት ነው። ሁለተኛ ለቀድሞው የእምቢታ አቋማችሁ ምርኮኛ ከመሆን ተላቃችሁ የትግራይ ሕዝብ ከጎረቤት የኤርትራ ሕዝብ ጋር በሰላምና በመከባብር እንዲኖሩ በማሰብ በቅድሚያ የድንበር ኮሚሽን ውሳኔ መቀበልና ከሉዓላዊ የኤርትራ መሬት መውጣት ነው። ላለፉት ሃያ ዓመታት ያመለጣችሁን ዕድል ይኽን ታሪካዊ እርምጃ መውሰድ በሁለቱ መንግሥታትና በኤርትራና በኢትዮጵያ(ትግራይ) ሕዝብ መካከል ለወደፊት በሰላምና በመከባበር እንዲኖሩ የሚያስችል የመጀመሪያው ታሪካዊ ምዕራፍ ሊሆን ይችላል።

**11.** ይኽን ቆራጥ እርምጃ ከወሰዳችሁ የኢትዮ-ኤርትራ አዲስ የሰላም ምዕራፍ በመክፈት ባለፉት ሃያ ዓመታት የባከነውን ጊዜ ባፋጣኝ ለመተካትና ሕዝቦቻችንን ከድህነት ለማላቀቅ ወሳኝ ሚና መጫወት ትችላላችሁ። በተለይም ለወጣቱ ስራ የሥራ ዕድል የሚጥሩ የኢኮኖሚና የልማት ፕሮጀክቶች እንዲሁም በደንበር አካባቢ ለሚኖሩ ለተጎዱት የሁለቱ ሃገራት ሕዝቦች ኑሮ ለማሻሻል ሰፊ በር ይከፍታል። ይኽን ሳታደርጉ የጦርነት ጥሪ ማስተጋብቱን እንደድሮው ከቀጠላችሁ በሁለቱ ሃገሮች መካከል ከፍተኛ ውጥረት እና ደም መፋሰስ ሊያስከትል ይችላል። ከዚህ ሳትታቀቡ እንዲሁ ከኤርትራ ጋር ቅርብ ግንኙነት እንፈልጋለን በማለት የምትደሰኩሩት ለሕዝብ ግንኙነት ፍጆታ ካልሆነ በስተቀር ለሁለቱ ጎረቤት ሕዝብ በሰላም የመኖር ዕድል ምንም ፋይዳ አይኖረውም።

"በኤርትራውያንና ኤርትራ ላይ የፈጸመችሁት ግፍ አልረሳነውም ፤ እንዴት ይረሳል?!"

ረዘነ ተስፋይ
ዋሽንግተን ዲ.ሲ.

**...የቀድሞ የወያኔ መሪዎች ማወቅ የተሳናችሁ ትልቅ ምሥጢር ስለሳዋ ሥልጠና ማዕከል ነው በሳዋ ከሁሉም ብሄሮች የተወጣጡት ምልምል ወጣቶች ከአካዳሚያዊና ወታደራዊ ሥልጠና ከመቅሰም ባሻገር በ18 ወራት ሳዋ ቆይታቸው የእርስ በርስ መከባበርና መቻቻል፣ የአብሮ መኖር አመለካከት ማዳበራቸውና አንድነታቸው ነው...**